# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# በውኃ ምንጭ ዳር ያለችው ሴት።


ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።




ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ በሳምራዊያን መንገድ ሲጓዙ ነበረ። ሲካር በሚባል ከተማ መሃከል ደረሱ።





በዚያ የውኃ ምንጭ ነበረ ፤ የሲካር ሰዎች ውኃን ያወጡበት የነበረ፡፡ ያዕቆብ ፣ የእስራኤላዊያን አባት ከብዙ አመታት በፊት የቆፈረው መሬት ነው፡፡
3
የከሰዓቱ መጀመሪያ ጸሀያማ እና ሞቃት ነበረ፡፡ እጅግ አድካሚ በሆነ ሁኔታ ፣ ደቀመዛሙርቱ ምግባቸውን ሊገዙ ወደ ሲካር በሄዱበት ሰዓት ፣ ኢየሱስ በውኃው ምንጭ ዳር ተቀመጠ፡፡
4
ኢየሱስ ብቻውን ነበረ - ነገር ግን ለረዥም ጊዜ አልነበረም፡፡ በሲካር ትኖር የነበረች ሴት ውኃ ልታወጣ መጣች፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አላት ፣” ውኃ አጠጪኝ”፡፡
5
ሴቲቱም ተደንቃ ነበረ፡፡ እንዲህም አለች፣ “እንዴት አንተ እንዲህ አልከኝ ፣ አይሁዳዊ ስትሆን ሳምራዊ ከምሆን ከእኔ ውኃን እንዴት ጠየቅከኝ?” በእነዚያ ቀናት ፣ አይሁዳዊያኑ ከሳምራዊያን ጋር አይተባበሩም ነበረ፡፡
6
እርሷ ምንአልባትም ኢየሱስ ይሄንን ሲላት እጅግ ተደንቃ ነበረ ፤ “ እኔ ማን እንደሆንሁ ብታውቂ፣ ሕያው ውኃን ትጠይቂኝ ነበረ፡፡”
7
ሴቲቱም እንዲህ ስትል ለኢየሱስ መለሰችለት ፤ “ጌታ ሆይ ፣ ምንም አይነት መቅጃ አልያዝክም፡፡ ምንጩም እጅግ ጥልቅ ነው፡፡ ያንን ሕያው ውኃ ከየት ልታገኘው ትችላለህ? ይሄንን ምንጭ ከሰጠን ከያዕቆብ ትበልጣለህን?”
8

ኢየሱስም ለሴቲቱ አላት ፣ “ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ዳግም ይጠማል፡፡ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ፈጽሞ አይጠማም፡፡ እኔ የምሰጠው ውኃ የዘላለምን ሕይወት የሚሰጥ ምንጭ ይሆናል፡፡” ሴቲቱም አለች “ጌታ ሆይ እባክህን ይሄንን ውኃ ስጠኝ”



9

ኢየሱስም ባሏን ጠርታ እንድትመጣ ነገራት፡፡ “ባል የለኝም አለችው፡፡” ኢየሱስም “አምስት ባሎች ነበሩሽ” አላት፡፡ “አሁን አብሮሽ ያለውም ባልሽ አይደለም” አላት፡፡



10

ሴቲቱም ኢየሱስ ነብይ መሆኑን አወቀች፡፡ እግዚአብሔር የት መመለክ እንዳለበትም ልትከራከው ጀመረች፤ በኢየሩሳሌም ነው ወይስ በሳምራዊያን ቅዱስ ተራራ ላይ? ኢየሱስም እንዲህ አለ “እውነተኛ አምላኪዎች እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ የሚያመልኩ ናቸው፡፡”



11

ሴቲቱም ለኢየሱስ አለችው፣ “መሲሕ እንደሚመጣ አውቃለሁ፡፡ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል፡፡” ኢየሱስም አላት “አሁን ይሄንን የምናገርሽ እርሱ እኔ ነኝ፡፡” ከዚያም በኋላ ፣ ደቀመዛሙርቱ ተመለሱ፡፡ ሴቲቱ ያንን እጅግ ውድ የውኃ እንስራ ጥላ ወደ ከተማው ሮጠች፡፡



12

“እስከዛሬ ድረስ የሰራሁትን ነገር የነገረኝን ሰው ኑና እዩት” ሴቲቱ ለሲካር ሰዎች የተናገረችው ነው፡፡ “ይሔ ክርስቶስ ይሆንን?” ሰዎቹ ከተማውን ለቀቁትና ኢየሱስን በራሳቸው አዩት፡፡



13

በመሃል፣ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ምግቡን እንዲበላ ነገሩት፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ አለ “የእኔ ምግብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግና ስራውን መፈጸም ነው፡፡” የእርሱ ስራ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ነበረ፡፡



14



ብዙ ሳምራዊያንም
በሴቲቱ ቃል የተነሳ
በኢየሱስ አመኑ፡፡
ከእነርሱም ጋር
እንዲኖር ግድ አሉት፡፡
እርሱም ከእነርሱጋ
ለሁለት ቀን ቆየ፡፡
እጅግ ብዙዎቹ
በኢየሱስ የራሱ ቃላት
አመኑ፡፡ እንዲህም
አሉ "......በራሳችን
ሰምተናል እናም ይሄ
የአለም መድኃኒት
ክርስቶስ መሆኑን
እናውቃለን፡፡"



በውኃ ምንጭ ዳር ያለችው ሴት፡፡

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዩሐንስ 4

**"የቃልህ ፍቺ ያበራል."**
**መዝሙረ ዳዊት 119:130**



# መጨረሻ

47 60



ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር "ኃጢአት" ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16